| | |
|---|---|
| ዐይነት ፤ | ዐምደኛ ፡ ጽሑፍ ፤ "አኃዛውያን ፡ ልቅሞች ። " |
| ርእስ ፤ | "የዓለም ፡ አህጉራት ፡ ስሞች ፡ በዐማርኛ ፡ እና ፡ በእየራሳቸው ፡ አጠራር ። " |
| ደራሲ ፤ | "ሥልጡንሕዝብና" ፡ መዜንው ። |
| ዕለት ፤ | መስከረም ፡ 2012 ፡ ዓ.ም. ። |
| ዝግጅት ፤ | ክለሳ ፡ 1_20120116 ። |
| መጽሔት ፤ | "ሥልጡንሕዝብና" ፡ መዜንው ፥ ቍ.2012-001 ። |
| ማስታወሻ ፤ | (በ"ሀ-ለ-ሐ-መ..." ፡ ተራ ። ) |
| ማሳሰቢያ ፤ | (ስሕተቶች ፡ በተገኙ ፡ ወይ ፡ በተጠቈሙ ፡ ቍጥር ፡ ታርመው ፥ ዝርዝራቸው ፡ ዳግመኛ ፡ ባዲስ ፡ ክለሳ ፡ ይወጣል ። ) |

# አኃዛውያን ፡ ልቅሞች ።

statistical data | données statistiques | بيانات احصائية

## የዓለም ፡ አህጉራት ፡ ስሞች ፡ በዐማርኛ ፡ እና ፡ በእየራሳቸው ፡ አጠራር ።

(በ"ሀለሐመ" ፡ ተራ)

———

የዓለም ፡ አህጉራት [1] ፡ አጠራር ፡ በዐማርኛ ፡ ገና ፡ በሚገባ ፡ አልተደነባም ። በተለይ ፡ በኢትዮጵያውያን ፡ ማወራኛዎች ፡ ኹሉን ፡ ዐይነት ፡ አጠራር ፡ ይሰማል ፤ ይነበባል ። ለምሳሌ ፦

- አንዱ ፥ ዐማርኛን ፡ ተከትሎ ፥ "ቱርክ" ፡ ሲል ፡ ሌላው ፥ እንግሊዝኛን ፡ ተከትሎ ፥ "ተርኪ" ፡ ይላል ፥ ሀገሩ ፡ ግን ፡ ራሱን ፡ "ቱርኪየ / Türkiye" ፡ ብሎ ፡ ይጠራል ፤
- አንዱ ፥ ዐማርኛን ፡ ተከትሎ ፥ "ጀርመን" ፡ ሲል ፡ ሌላው ፥ እንግሊዝኛን ፡ ተከትሎ ፥ "ጀርመኒ" ፡ ይላል ፥ ሀገሩ ፡ ግን ፡ ራሱን ፡ "ዶይችላንድ / Deutschland" [2] ፡ ብሎ ፡ ይጠራል ፤
- አንዱ ፥ ዐማርኛን ፡ ተከትሎ ፥ "ግብጽ" ፡ ሲል ፡ ሌላው ፥ እንግሊዝኛን ፡ ተከትሎ ፥ "ኢጂፕት" ፡ ይላል ፥ ሀገሩ ፡ ግን ፡ ራሱን ፡ "ምጽር / مصر" [3] ፡ ብሎ ፡ ይጠራል ፤
- አንዱ ፥ ዐማርኛን ፡ ተከትሎ ፥ "ነምሳ" ፡ ሲል ፡ ሌላው ፥ እንግሊዝኛን ፡ ተከትሎ ፥ "አስትሪያ" ፡ ይላል ፥ ሀገሩ ፡ ግን ፡ ራሱን ፡ "ኧስተርራይሽ / Österreich" [4] ፡ ብሎ ፡ ይጠራል ፤ ወዘተርፈ ፡ ... ።

ሥራን ፡ በዚህ ፡ ዝብርቅርቅ ፡ ውስጥ ፡ መቀጠሉ ፥ ብሎ ፡ ብሎ ፡ ለሀገራዊ ፡ ክስረት ፡ መዳረጉ ፡ ስለማይቀር ፥ ካኹኑ ፡ ሥርዐት ፡ ለማስያዝ ፡ መሞከር ፡ ይገባል ።

ለረዥም ፡ ዘመን ፥ በኢትዮጵያ ፡ ሕጋዊ ፡ መንግሥት ፡ አለመኖሩና ፥ የሥልጣን ፡ ተገቢነት ፡ መታጣቱ ፥ ችግሩን ፡ እጅግ ፡ አሳሳቢ ፡ ደረጃ ፡ አድርሶታል ። ተማሪም ፡ ባለሚያም ፡ በራሱ ፡ ሀገራዊ ፡ ቋንቋ ፡ እኩል ፡ አላዋቂ ፡ በኾነበት ፡ ኹኔታ ፡ የሚሠራ ፡ ሥራ ፡ ኹሉ ፡ "የእንቧይ ፡ ካብ" ፡ ስለሚኾንና ፥ ስለሚፈርስ ፥ መጨረሻውን ፥ "አንድ ፡ ፊቱን ፥ ደኅና ፡ የተደነባውንና ፡ የታደበውን ፡ የውጭ ፡ ቋንቋ ፡ ይዘን ፡ ብንቀጥል ፡ አይሻለንምን ፧ " ፡ ወደሚለው ፡ የሰነፍ ፡ መፍትሔ ፡ እንዳናዘነብልና ፡ ሀገራዊ ፡ ህልውናችንን ፡ አደጋ ፡ ላይ ፡ እንዳንጥል ፡ ያሠጋል ።

በሀገረ ፡ ኢትዮጵያ ፥ ሕጋዊ ፡ መንግሥት ፡ በሕጋዊ ፡ ሕገ ፡ መንግሥት ፡ እስኪሠየም ፡ ድረስ ፥ ኹላችን ፡ በእያለንበትና ፡ በእየሥራ ፡ መስካችን ፡ የተቻለንን ፡ ያኽል ፡ ዐማርኛችንን ፡ እያስተካከልን ፡ ሥራን ፡ መቀጠሉ ፡ የተሻለው ፡ ማማረጫ ፡ ይኾንልናል ።

***ሥልጡንሕዝብና*** ፡ መዜንውም ፥ ይህኑ ፡ ሐሳብ ፡ ተቀብሎ ፥ "**ዐውደ ፡ ቀለም**" ፡ በተባለው ፡ የጽሑፍ ፡ ማምረቻ ፡ መግበር ፡ በመታገዝ ፥ የሀገርና ፡ የቦታ ፡ ስሞችን ፡ በትኽክለኛ ፡ መንገድ ፡ የመመዝገብን ፡ ሥራ ፡ ቀጥሏል ። የደረሰባቸውን ፡ ውጤቶች ፡ ኹሉ ፡ ይፋ ፡ እያወጣም ፡ ለሕዝብ ፡ በመናኘት ፥ ሀገራዊ ፡ እና ፡ ሕዝባዊ ፡ ሱታፌያችንን ፡ ለማቀልጠፊ ፡ የበኩሉን ፡ አስተዋፅኦ ፡ እንሆ ፡ ማበርከቱን ፡ ቀጥሏል ።

በተከታታይ ፡ ዝግጅቶች ፡ የዓለም ፡ ሀገሮች ፡ ስሞችን ፥ ከዚያም ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ በማተኮር ፥

---

1 <u>**አህጉራት**</u> ፤ ሀገሮች ፡ ማለት ፡ እንጂ ፡ የብሶች ፡ ማለት ፡ አለመኾኑን ፡ ልብ ፡ ይሏል ፡ (አንድ ፡ ሀገር ፣ ኹለት ፡ አህጉር ፣ ብዙ ፡ አህጉራት) ።

2 <u>**ዶይችላንድ**</u> ፤ ብሔረ ፡ ዶይች ፡ ወይም ፡ የዶይቾች ፡ ምድር ። ዶይች ፡ በመኻል ፡ አውሮፓ ፡ የሚኖሩ ፡ ጎሳዎች ፡ የወል ፡ ስም ፤ ሌላው ፡ ስማቸው ፡ "ጌርማን" ።

3 <u>**ምጽር**</u> ፤ ምስር ፡ ወይም ፡ ግብጽ ፥ የምጽራይም ፡ ሀገር ፡ (ዘፍ. ፥ 10 ፥ 6 ፤ *የካምም ፡ ልጆች ፡ ኵሽ ፣ ምጽራይም ፣ ፉጥ ፣ ከነዓን ፡ ናቸው ።* )

4 <u>Österreich / ኧስተርራይሽ</u> ፤ "ምሥራቃዊ ፡ መንግሥት" ።


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2012 ፡ ዓ.ም. ።

ከክፍለ ፡ ሀገር ፡ አንሥቶ ፡ እስከ ፡ ወረዳና ፡ ዋና ፡ ዋና ፡ ከተሞቻቸው ፡ የሚዘረዘሩትን ፡ የዘንዱ ፡ ስሞች ፡ በትኽክለኛ ፡ አጠራራቸውና ፡ አጻጻፋቸው ፡ አሟልተን ፡ እናቀርባለን ። በዐዲሱ ፡ የቢጋር ፡ ዐምዳችንም ፥ የተቻለውን ፡ ያኽል ፡ መረጃውን ፡ በቢጋር ፡ በመከሠት ፥ ማንኛውንም ፡ ወገን ፡ በረገዱ ፡ የትኽክለኛ ፡ ዕውቀት ፡ ባለቤት ፡ ለማድረግ ፡ የተቻለውን ፡ ኹሉ ፡ እንጥራለን ።

በተለይ ፡ የውጭ ፡ ሀገሮችን ፡ የስም ፡ አጠራር ፥ በተቻለ ፡ መጠን ፡ ሀገሩ ፡ ራሱን ፡ በሚጠራበት ፡ አጠራር ፡ ለመመዝገብ ፡ ሞክረናል ። ነገር ፡ ግን ፥ ጥንታዊ ፡ ያማርኛ ፡ አጠራር ፡ ላላቸው ፡ ሀገሮች ፥ ዐማርኛውን ፡ አጠራር ፡ ከአገሬው ፡ አጠራር ፡ ጋራ ፡ ዐብረን ፡ ዘርዝረናል ። ለምሳሌ ፡—

ነምሳ / ኧስተርራይኽ ▶ Austria / Österreich

እንደዚሁ ፥ የቈየ ፡ ያማርኛ ፡ አጠራር ፡ የሌላቸውን ፡ ዐዳዲስ ፡ ሀገሮች ፡ ራሳቸውን ፡ በሚጠሩበት ፡ አጠራራቸው ፡ ብቻ ፡ መዝግበናቸዋል ፤ ለምሳሌ ፡—

ካናዳ ▶ Canada

ስማቸው ፡ ከተጸውዖ ፡ ስምነት ፡ ጋራ ፡ የሚተረጐም ፡ ጠባይ ፡ ቢኖረው ፡ ደግሞ ፥ ፈጽመን ፡ ወዳማርኛ ፡ በመተርጐም ፡ መዝገበነዋል ፤ ለምሳሌ ፡—

የተባበሩት ፡ የአሜሪካ ፡ ኹነቶች ▶ United States of America

ስማቸው ፡ ካንድ ፡ ቃል ፡ በላይ ፡ ያላቸውን ፡ ደግሞ ፡ በሠረዝ ፡ በማያያዝ ፡ ልንጽፋቸው ፡ እንችላለን ፤ ይህን ፡ ማድረጉ ፡ ለፊደል ፡ ጥንቀቃ ፡ ያመቻል ። ለምሳሌ ፡—

የተባበሩት ፡ የአሜሪካ ፡ ኹነቾት

የሚለውን ፡

የተባበሩት-የአሜሪካ-ኹነቾት

ብለን ፡ ብንጽፈው ፥ ከሦስት ፡ ቃላት ፡ ይልቅ ፡ ባንድ ፡ ቃልነት ፡ ተመዝግቦ ፥ የፊደል ፡ ጥንቀቃው ፡ በሦስት ፡ ረድፎች ፡ ከሚደረግ ፡ ይልቅ ፡ ባንድ ፡ ቃልነቱ ፡ ባንድ ፡ ጊዜ ፡ ሊደረግ ፡ ይችላል ።

የሮማይስጥ ፡ ጸሕፍ ፡ ወይም ፡ የምዕራባውያን ፡ ጸሕፍ ፡ ፊደሎችን ፡ "uppercase" ፡ እና ፡ "lowercase" ፡ ብሎ ፥ የተጸውዖ ፡ ስሞችን ፡ በ"uppercase" ፡ ፊደል ፡ በማስገምር ፥ ከሌሎች ፡ ስም ፡ በቀላሉ ፡ ይለያቸዋል ፤ ይህ ፡ ዘዴ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ፊደል ፡ አይገኝምና ፥ ኹለት ፡ ሦስት ፡ ቃላትን ፡ የያዙ ፡ ስሞችን ፡ በሠረዝ ፡ አያይዞ ፥ ባንድ ፡ ቃልነት ፡ እንለያቸው ፡ የሚለው ፡ ዘዴ ፥ ለጊዜው ፡ ጥሩ ፡ ማማረጫ ፡ ይኾናል ። የተሻለ ፡ ሐሳብ ፡ ወይ ፡ ዘዴ ፡ ቢኖር ፡ በደስታ ፡ እንቀበለዋለን ።

ያሠራራችን ፡ ዝርዝር ፡ ስልት ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ በማመዛዘኛ ፡ መልክ ፡ ይወጣል ።

ሥራው ፡ መቼም ፡ ቢኾን ፡ ፍጹም ፡ ስለማይኾን ፥ ጕዳዩ ፡ የሚያሳስባቸው ፡ ኹሉ ፡ ከሥራ ፡ ለመሳተፍም ፡ ኾነ ፥ አስተያየትን ፡ ለመቸር ፤ ስሕተትን ፡ ለመጠቈም ፥ በእ-ጦማር ፡ አድራሻችን ፡ ወይም ፡ በስልክ ፡ ቍጥራችን ፡ ሊያደርሱልን ፡ እንደሚችሉ ፡ በትሕትና ፡ እናሳስባለን ።

ለጊዜው ፡ የተዘረዘሩት ፡ ከሞላ ፡ ጐደል ፡ የ 210 ፡ ሀገሮች ፡ ስሞች ፡ ብቻ ፡ ናቸው ። ይህ ፡ የመግመሪያ ፡ ክለሳ ፡ እንደ ፡ መኾኑ ፡ መጠን ፥ ስሕተቶች ፡ በታረሙና ፡ ጕድለቶች ፡ በተሟሉ ፡ ቍጥር ፥ ባዲስ ፡ ክለሳ ፡ ይተካል ።

የሥራው ፡ መድረሻ ፡ ዐላማ ፥ በተለይ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ማወራኛዎች ፡ በፊደልም ፤ በትርጕምም ፡ ጥንቁቅ ፡ እና ፡ ወጥ ፡ በኾነ ፡ ግስ ፡ መሥራትን ፡ ደንባችን ፡ በማድረግ ፥ ሥራችን ፡ ርስ ፡ በርሱ ፡ ከመጣረስ ፡ ይልቅ ፡ ተባብሮ ፥ ርስ ፡ በርሱ ፡ ከመጣጣል ፡ ይልቅ ፡ ተደጋግፎ ፥ ሀገራዊ ፡ አስተዋፅኦው ፡ እንዲቀለጥፍ ፡ ነውና ፥ አርኣያነቱን ፡ ኹሉም ፡ በቀና ፡ መንፈስ ፡ ይቀበሉታል ፡ ብለን ፡ እናምናለን ።

*(ዝርዝሩን ፡ እሚቀጥለው ፡ ገጽ ፡ ይመለከቷል ።)*

| የሀገር ፡ ስም [በራስ ፡ አጠራር ፡ ወይም ፡ በዐማርኛ] | ሀገር [በራስ ፡ አጠራር ፡ ወይም ፡ በእንግሊዝኛ] | መዲና [በራስ ፡ አጠራር ፡ ወይም ፡ በዐማርኛ] | መዲና [በራስ ፡ አጠራር ፡ ወይም ፡ በእንግሊዝኛ] |
|---|---|---|---|
| ሀዪቲ | Haiti | ፖር ፡ ኦ ፡ ፕሪንስ | Port-au-Prince |
| ኤሌዳ/ሄላስ/ግሪክ | Elleda/Hellás/Greece | አቴና | Athens |
| ህንድ/ብሐራት | India/Bharat | ዐዲስ ፡ ዴልሂ | New Delhi |
| ሆላንድ/ኔዴርላንድ | Nederland | አምስተርዳም | Amsterdam |
| ሆንዱራስ | Honduras | ቴጉሲጋልፓ | Tegucigalpa |
| ሆንግ ፡ ኮንግ | Hong Kong | ሆንግ ፡ ኮንግ | Hong Kong |
| ሉብናን/ሊባኖስ | Lubnen/Lebanon | በይሩት | Beirut |
| ሉክሰምቡርግ | Luxembourg | ሉክሰምቡርግ | Luxembourg |
| ሊሽተንሽታይን | Liechtenstein | ሊሽተንሽታይን | Liechtenstein |
| ሊብያ | Libya | ጠራቡሉስ/ትሪፖሊ | Tripoli |
| ሊዬቱቫ/ሊቱአንያ | Lietuva/Lithuania | ቪልኒዩስ | Vilnius |
| ላትቪያ | Latvia | ሪጋ | Riga |
| ላኦ | Lao/Laos | ቪዬንትያን | Vientiane |
| ላይቤርያ | Liberia | ሞንሮቪያ | Monrovia |
| ሌሶቶ | Lesotho | ማሴሩ | Maseru |
| መውሪታንያ | Mauritania | ነዋቅሾት | Nouakchott |
| መግሪብ | Maghrib/Morocco | ሪባጥ | Rabat |
| ሚያንማር | Myanmar | ራንጉን | Rangoon |
| ማሊ | Mali | ባማኮ | Bamako |
| ማላዊ | Malawi | ሊሎንጔ | Lilongwe |
| ማሌዥያ | Malaysia | ኳላ ፡ ሉምፑር | Kuala Lumpur |
| ማልታ | Malta | ቫሌታ | Valletta |
| ማርሻል ፡ ደሴቶች | Marshall Islands | ናዎኤሮ / ናውሩ | Nauru |
| ማይክሮኔዥያ/ንኡሳን ፡ ደሴቶች | Micronesia | ኮሎኒያ | Colonia |
| ማዳጋስካራ | Madagascar | አንታናናሪቮ | Antananarivo |
| ማጊያሮርሳግ/ሁንጋርያ | Hungary | ቡዳፔሽት | Budapest |
| ምስር/ግብጽ | Egypt | ኧልቃሂራ/ቃሂራ | Cairo |
| ሞልዲቭዝ/ዲቬሂ ፡ ራጄ | Maldives | ማሌ | Male |
| ሞልዶቫ | Moldova | ኪሺኔቭ | Chisinau |
| ሞሪሺየስ | Mauritius | ሉዊ ፡ ወደብ | Port Louis |
| ሞናኮ | Monaco | ሞናኮ | Monaco |
| ሞንትሴራት | Montserrat | ፕሊሙት | Plymouth |
| ሞንጎልያ | Mongolia | ኡላን ፡ ባቶር | Ulan Bator |

| የሀገር ፡ ስም [በራስ ፡ አጠራር ፡ ወይም ፡ በዐማርኛ] | ሀገር [በራስ ፡ አጠራር ፡ ወይም ፡ በእንግሊዝኛ] | መዲና [በራስ ፡ አጠራር ፡ ወይም ፡ በዐማርኛ] | መዲና [በራስ ፡ አጠራር ፡ ወይም ፡ በእንግሊዝኛ] |
|---|---|---|---|
| ሞዛምቢክ | Mozambique | ማፑቶ | Maputo |
| ሟንግ ፡ ታይ/ታይላንድ | Thailand | ባንኮክ | Bangkok |
| ሩስያ/መስኮብ | Russia | ሞስኮቫ | Moscow |
| ሬፑብሊክ ፡ ዴሞክራቲክ ፡ ዱዩ ፡ ኮንጎ/ኮንጎ ፡ ሥልጡንሕዝባዊ ፡ ሬፑብሊክ | République Démocratique du Congo | ኪንሻሳ | Kinshasa |
| ሮማንያ | Romania | ቡካሬስቲ | Bucharesti |
| ሯንዳ | Rwanda | ኪጋሊ | Kigali |
| ሰሎሞን ፡ ደሴቶች | Solomon Islands | ሆኒያራ | Honiara |
| ሰሜን ፡ መቄዶንያ/መቄዶንያ | North Macedonia/Macedonia | ስኮፕዬ | Skopje |
| ሰሜን ፡ ኮርያ | North Korea | ፕዮንግያንግ | Pyongyang |
| ሱሪናም | Suriname | ፓራማሪቦ | Paramaribo |
| ሱዳን | Sudan | ኀርጡም | Khartoum |
| ሲንት ፡ ማርተን | Sint Maarten | ሲንት ፡ ማርተን | Sint Maarten |
| ሲንጋፑር | Singapore | ሲንጋፑር | Singapore |
| ሲዬራ ፡ ሌዮን | Sierra Leone | ፍሪታውን | Freetown |
| ሳሞዋ | Samoa | አፒያ | Apia |
| ሳን ፡ ማሪኖ | San Marino | ሳን ፡ ማሪኖ ፡ ከተማ | San Marino Citta |
| ሳኦ ፡ ቶሜ ፡ እና ፡ ፕሪንቺፔ | Sao Tome and Principe | ሳን ፡ ማሪኖ ፡ ከተማ | Sao Tome |
| ሳዑድያ ፡ ዐረብያ | Saudi Arabia | ሪያድ/ሪያዽ | Riyadh |
| ሴኔጋል | Senegal | ዳካር | Dakar |
| ሴይሼልዝ | Seychelles | ቪክቶሪያ | Victoria |
| ስሎቫክያ | Slovakia | ብራቲስላቫ | Bratislava |
| ስሎቬንያ | Slovenia | ሉብሊያና | Ljubljana |
| ስሪ ፡ ላንካ | Sri Lanka | ኮሎምቦ | Colombo |
| ስርብያ | Serbia | ቤዎግራድ | Béograd |
| ስቬሪገ/ስዊድን | Sweden | ስቶክሆልም | Stockholm |
| ስዊስ | Switzerland | ቤርን | Bern |
| ስዋዚላንድ/ካንጓኔ | Swaziland/Kangwané | እምባባኔ | Mbabané |
| ሶማልያ | Somalia | ሙቅዲሾ/ሞቃድሾ/መቅደሹ | Muqdisho / Mogadishu |
| ሶርያ | Syria | ደማስቆ | Damascus |
| ሽኪፔርያ/አልባንያ | Shqipëria/Albania | ቲራና | Tirana |
| ቀጠር | Qatar | ደውሐ | Doha |
| ቅዱስ ፡ ቪንሰንት ፡ | Saint Vincent | ኪንግስታውን | Kingstown |


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፡ 2012 ፡ ዓ.ም. ።

| የሀገር ፡ ስም [በሌላ ፡ አጠራር ፡ ወይም ፡ በዐማርኛ] | ሀገር [በሌላ ፡ አጠራር ፡ ወይም ፡ በእንግሊዝኛ] | መዲና [በሌላ ፡ አጠራር ፡ ወይም ፡ በዐማርኛ] | መዲና [በሌላ ፡ አጠራር ፡ ወይም ፡ በእንግሊዝኛ] |
|---|---|---|---|
| እና ፡ ግሬናዲንዝ/ሴንት ፡ ቪንሰንት ፡ እና ፡ ግሬናዲንዝ | and the Grenadines | | |
| ቅዱስ ፡ ኪትስ ፡ እና ፡ ኔቪስ/ሴንት ፡ ኪትስ ፡ እና ፡ ኔቪስ | Saint Kitts and Nevis | ባስ ፡ ቴር | Basse Terre |
| ቅድስት ፡ ሉስያ/ሴንት ፡ ሉስያ | Saint Kitts and Nevis | ካስትሪዝ | Castries |
| ቡልጋርያ | Bulgaria | ሶፊያ | Sophia |
| ቡሩንዲ | Burundi | ቡጁምቡራ | Bujumbura |
| ቡርኪና ፡ ፋሶ | Burkina Faso | ዋጋዱጉ | Ouagadougou |
| ቡታን | Bhutan | ቲምፑ | Thimphu |
| ባሀማስ | Bahamas | ናሳው | Nassau (on New Providence) |
| ባሕረይን | Bahrain | መናማ | Manama |
| ባርቤዶስ | Barbados | ብሪጅታውን | Bridgetown |
| ባንግላዴሽ | Bangladesh | ዳካ | Dhaka |
| ቤሊዝ | Belize | ቤልሞፓን | Belmopan |
| ቤላሩስ | Bélarus | ሚንስክ | Minsk |
| ቤልዢክ/ቤልጊየ | Belgique/Belgie | ብሩክሴል | Bruxelles |
| ቤርሙዳ | Bermuda | ሀሚልተን | Hamilton |
| ቤኒን | Benin | ዐዲስ ፡ ወደብ/ፖርቶ ፡ ኖቮ | Porto Novo |
| ብሩኔይ | Brunei | በንደር ፡ ሴሪ ፡ ቤጋዋን | Bender Séri Bégawan |
| ብራዚል | Brasilia | ብራዚልያ | Brasil/Brazil |
| ቦሊቭያ | Bolivia | ላ ፡ ፓዝ | La Paz |
| ቦትስዋና | Botswana | ጋቦሮኔ | Gaborone |
| ቦዝንያ ፡ ሄርዜጎቪና | Bosnia and Herzegovina | ሳራዬቮ | Sarajevo |
| ቪዬትናም | Vietnam | ሀኖይ | Hanoi |
| ቫኗቱ | Vanuatu | ፖርት ፡ ቪላ/ቪላ ፡ ወደብ | Port Vila |
| ቬኔዝዌላ | Venezuela | ካራካስ | Caracas |
| ተርክስ ፡ እና ፡ ካይኮስ ፡ ደሴቶች | Turks and Caicos Islands | ኮክበርን ፡ ታውን/ኮክበርን ፡ ከተማ | Cockburn Town |
| ቱርኪየ | Türkiye/Turkey | አንካራ | Ankara |
| ቱርክሜኒስታን | Turkmenistan | አሽኻባድ | Ashgabat |
| ቱቫሉ | Tuvalu | ቫያኩ/ፉናፉቲ | Vaiaku/Funafuti |
| ቱኒስያ | Tunisia | ቱኒስ | Tunis |
| ቲሞር ፡ ሌስቴ/ምሥራቅ ፡ ቲሞር | Timor-Leste/East Timor | ዲሊ | dili |
| ታንዛንያ | Tanzania | ዶዶማ | Dodoma |
| ታይዋን | Taiwan | ታይፔይ | Taipei |
| ታጂኪስታን | Tajikistan | ዱሻንቤ | Dushanbe |
| ትሪኒዳድ ፡ እና ፡ ቶባጎ | Trinidad and Tobago | ፖርት ፡ ኦፍ ፡ ስፔይን | Port of Spain |
| ቶንጋ | Tonga | ኑኩአሎፋ | Nukualofa |
| ቶጎ | Togo | ሎሜ | Lome |
| ቺሌ | Chile | ሳንቲያጎ ፡ ዴ ፡ ቺሌ | Santiago de Chile |
| ቻይና/ሲን/ዡንግዎ | China/Zhongguo | ቤይጂንግ | Beijing |
| ቻድ | Chad | ንጃሜና | N'Djamena |
| ቼካ ፡ ሬፑብሊካ | Czech Republic | ፕራሀ | Prague |
| ኒካራጓ | Nicaragua | ማናጓ | Managua |
| ኒው ፡ ዚይለንድ/ዐዲስ ፡ ዚይለንድ | New Zealand | ዌሊንግተን | Wellington |
| ኒዤር | Niger | ኒያሜይ | Niamey |
| ኒፖን/ኒሆን/ጃፓን | Nippon/Nihon/Japan | ቶኪዮ | Tokyo |
| ናሚብያ | Namibia | ዊንድሆክ | Winhoek |
| ናዎኤሮ/ንውሩ | Naoero/Nauru | ያሬን ፡ ዲስትሪክት/ያሬን ፡ ወረዳ | Yaren District |
| ናይጄርያ | Nigeria | አቡጃ | Abuja |
| ኔፓል | Nepal | ካትማንዱ | Kathmandu |
| ኖርገ/ኖርዌይ | Norway | ኦስሎ | Oslo |
| አሩባ | Aruba | ኦራንዠስታት | Oranjestad |
| አርማንያ/አርሜንያ/ሀያስታን | Armenia | ዬሬቫን | Yerevan |
| አርጄንቲና | Argentina | ቡኤኖስ ፡ አይሬስ | Buenos Aires |
| አንቲጓ ፡ እና ፡ ባርቡዳ | Antigua and Barbuda | ሴንት ፡ ጆንዝ | Saint John's |
| አንዶራ | Andorra | አንዶራ ፡ ላ ፡ ቬላ | Andorra la Vela |
| አንጎላ | Angola | ሏንዳ/ሉዋንዳ | Luanda |
| አንጕላ | Anguilla | ዘ ፡ ቫሌይ/ዘ ፡ ቫሌይ | The Valley |
| አውስትራልያ | Australia | ካንቤራ | Canberra |
| አዜርባይጃን | Azerbaijan | ባኩ | Baku |
| አፍጋኒስታን | Afghanistan | ካቡል | Kabul |
| ኡሩጓይ | Uruguay | ሞንቴቪዴዎ | Montevideo |
| ኡርዱን/ዮርዳኖስ | Jordan | ዐማን | Amman |


©ኢ..ሀ.ሥ.አ. ፥ 2012 ፡ ዓ.ም. ።

| የሀገር ፡ ስም [በራስ ፡ አጠራር ፡ ወይም ፡ በዐማርኛ] | ሀገር [በራስ ፡ አጠራር ፡ ወይም ፡ በእንግሊዝኛ] | መዲና [በራስ ፡ አጠራር ፡ ወይም ፡ በዐማርኛ] | መዲና [በራስ ፡ አጠራር ፡ ወይም ፡ በእንግሊዝኛ] |
|---|---|---|---|
| ኡክራይና | Ukraine | ኪዬቭ | Kiev |
| ኡዝቤኪስታን | Uzbekistan | ታሽኬንት | Tashkent |
| ኡጋንዳ | Uganda | ካምፓላ | Kampala |
| ኢራቅ | Iraq | በግዳድ/በኻዳድ | Baghdad |
| ኢራን/ፋርስ | Iran | ቴሀራን | Tehran |
| ኢስላንድ | Island/Iceland | ሬይክያቪክ | Reykjavik |
| ኢትዮጵያ | Ethiopia | ዐዲስ ፡ አበባ | Addis Abeba |
| ኢንዶኔዥያ | Indonesia | ጃካርታ | Jakarta |
| ኢጣልያ | Italy | ሮማ | Rome |
| ኤል ፡ ሳልቫዶር | El Salvador | ሳን ፡ ሳልቫዶር | San Salvador |
| ኤስቲ/ኤስቶንያ | Estonia | ታሊን | Tallinn |
| ኤስፓኛ | Spain | ማድሪድ | Madrid |
| ኤኳዶር | Ecuador | ኪቶ | Quito |
| ኤይር/አየርለንድ | Ireland | ዳብሊን | Dublin |
| እስራኤል | Israel | ኢየሩሳሌም | Yerushalaym |
| ኧልጀዘኢር | Algeria | ጀዘኢር | Alger |
| ኧስተርራይሽ/ነምሳ | Österreich | ቪዬና | Vienna |
| ኩራሳዉ | Curaçao | ቪለምሽታት | Willemstad |
| ኩባ | Cuba | ሀቫና | Havana |
| ኩክ ፡ ደሴቶች | Cook Islands | አቫሩአ | Avarua |
| ኩወይት | Kuwait | ኩወይት ፡ ከተማ | Kuwait City |
| ኪሪባቲ | Kiribati | ባይሪኪ | Bairiki |
| ኪርጊስታን | Kyrgyzstan | ቢሽኬክ | Bishkek |
| ኪፕሮስ/ቆጵሮስ | Kypros | ኒኮሲያ | Nicosia |
| ካሜሩን | Cameroon | ያውንዴ | Yaoundé |
| ካምፑቼያ | Cambodia | ፕኖም ፡ ፔን | Phnom Penh |
| ካቦ ፡ ቬርዴ | Cape Verde | ፕራያ | Praia |
| ካናዳ | Canada | ኦታዋ | Ottawa |
| ካዛኽስታን | Kazakhstan | አስታና | Astana |
| ካይማን ፡ ደሴቶች | Cayman Islands | ጆርጅታውን | Georgetown |
| ኬንያ | Kenya | ናይሮቢ | Nairobi |
| ክርና ፡ ጎራ/ሞንቴኔግሮ | Montenegro | ፖድጎሪካ | Podgorica |
| ኮሎምብያ | Colombia | ቦጎታ | Bogotá |
| ኮሞረስ/ገዙዙር ፡ ኧል ፡ ቀምር | Comoros | ሞሮኒ | Moroni |
| ኮስታ ፡ ሪካ | Costa Rica | ሳን ፡ ኾሴ | San Jose |
| ኮት ፡ ዲቯር | Côte d'Ivoire | አቢጃን | Abidjan |
| ኮንጎ ፡ ሬፑብሊክ | République du Congo | ብራዛቪል | Brazzaville |
| ኽርቫትስካ | Hrvatska/Croatia | ዛግሬብ | Zagreb |
| ዐዲስ ፡ ካሌዶንያ | Nouvelle Calédonie | ኑሜአ | Nouméa |

| የሀገር ፡ ስም [በራስ ፡ አጠራር ፡ ወይም ፡ በዐማርኛ] | ሀገር [በራስ ፡ አጠራር ፡ ወይም ፡ በእንግሊዝኛ] | መዲና [በራስ ፡ አጠራር ፡ ወይም ፡ በዐማርኛ] | መዲና [በራስ ፡ አጠራር ፡ ወይም ፡ በእንግሊዝኛ] |
|---|---|---|---|
| ዑማን | Oman | መስቀጥ | Masqat |
| ዚምባብዌ | Zimbabwe | ሐራሬ | Harare |
| ዛምብያ | Zambia | ሉሳካ | Lusaka |
| የመን | Yemen | ጸነዓዕ | Sana'a |
| የመካከለኛ ፡ አፍሪቃ ፡ ሬፑብሊክ | Central African Republic | ባንጊ | Bangui |
| የብሪታንያ ፡ ደናግል ፡ ደሴቶች | British Virgin Islands | ሮድ ፡ ታውን | Road Town |
| የተባበረው ፡ መንግሥት/ብሪታንያ | United Kingdom | ለንደን | London |
| የተባበሩት ፡ የአሜሪካ ፡ ኹነቶች | United States of America | ዋሺንግተን/ዋሺንተን | Washington |
| የተባበሩት ፡ የዐረብ ፡ ኢማራት ፡ መንግሥት/ደውለት ፡ ኧልኢማራት ፡ ኧልዐረቢያ ፡ ኧልሙታሒዳ | United Arab Emirates | አቡ ፡ ዷቢ/አቡ ፡ ዳቢ | Abu Dhabi |
| የፍራንስ ፡ ፖሊኔዥያ | Polynésie Française | ፓፔቴ | Papeete |
| ደቡብ ፡ ሱዳን | South Sudan | ጁባ | Juba |
| ደቡብ ፡ አፍሪቃ | South Africa | ፕሬቶሪያ | Pretoria |
| ደቡብ ፡ ኮርያ | South Korea | ሴኡል | Seoul |
| ዳንማርክ | Danmark | ኮፐንሀገን | Copenhagen |
| ዶሚኒካ | Dominica | ሮዞ | Roseau |
| ዶሚኒካ ፡ ሬፑብሊክ | Dominican Republic | ሳንቶ ፡ ዶሚንጎ | Santo Domingo |
| ጀርመን/ዶይችላንድ | Germany | ቤርሊን | Berlin |
| ጂቡቲ | Djibouti | ጂቡቲ | Djibouti |
| ጃማይካ | Jamaica | ኪንግስተን | Kingston |
| ጊኔ | Guinea | ኮናክሪ | Conakry |
| ጊኔ ፡ ቢሳዉ | Guinea-Bissau | ቢሳዉ | Bissau |
| ጊኔ ፡ ወገብጌ | Equatorial Guinea | ማላቦ | Malabo |
| ጋምብያ | Gambia | ባንጁል | Banjul |
| ጋቦን | Gabon | ሊብረ ፡ ቪል | Libreville |
| ጋና | Ghana | አክራ | Accra |
| ጋያና | Guyana | ጆርጅታውን | Georgetown |
| ግሪንላንድ/ካላሊት ፡ ኑናት | Kalaalit Nunaat/Grønland | ኑክ/ጎድታብ | Nuuk/Godthab |


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፡ 2012 ፡ ዓ.ም. ።

| የሀገር ፡ ስም [በሌስ ፡ አጠሬር ፡ ወይም ፡ በዐማርኛ] | ሀገር [በሌስ ፡ አጠሬር ፡ ወይም ፡ በእንግሊዝኛ] | መዲና [በሌስ ፡ አጠሬር ፡ ወይም ፡ በዐማርኛ] | መዲና [በሌስ ፡ አጠሬር ፡ ወይም ፡ በእንግሊዝኛ] |
|---|---|---|---|
| ግሩዥያ | Georgia | ትቢሊሲ | Tbilisi |
| ግሬናዳ | Grenada | ሴንት ፡ ጆርጅዝ | Saint George's |
| ጓቴማላ | Guatemala | ጓቴማላ ፡ ከተማ | Guatemala City |
| ፊሊፒናስ | Philippines | ማኒላ | Manilla |
| ፊንላንድ/ሱኦሚ | Finland | ሄልሲንኪ | Helsinki |
| ፊጂ | Fiji | ሱቫ | Suva |
| ፍልስጥኤም/ፊለስጢን | Palestine | አሪሐ/ኢያሪኮ | Jericho |
| ፍራንስ | France | ፓሪ/ፓሪስ | Paris |
| ፓላዉ | Palau | ኮሮር | Koror |
| ፓራጓይ | Paraguay | አሱንሲዮን | Asuncion |
| ፓናማ | Panama | ፓናማ ፡ ከተማ | Panama City |
| ፓኪስታን | Pakistan | እስላማባድ | Islamabad |
| ፓፓ ፡ ኒው ፡ ጊኒ/ፓፓ ፡ ዐዲስ ፡ ጊኒ | Papua New Guinea | ፖርት ፡ ሞርዝቢ | Port Moresby |
| ፔሩ | Peru | ሊማ | Lima |
| ፕዌርቶ ፡ ሪኮ | Puerto Rico | ሳን ፡ ኳን | San Juan |
| ፖልስካ/ፖላንድ | Poland | ቫርሻቫ | Warsaw |
| ፖርቱጋል | Portugal | ሊስቦን | Lisbon |


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2012 ፡ ዓ.ም. ።